- እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በሚታገሉት ላይ ምን ያደርስባቸዋል?

- ይቀጣቸዋል።

- እግዚአብሔር ሰዎችን በምድር ላይ በልዩ ልዩ ቦታዎች በተናቸው።

- አንዳንድ ሰዎች ከባቤል ቅርብ ወደ ሆኑ ቦታዎች ሰፈሩ።

- አንዳንድ ሰዎች ከባቤል ርቀው ሰፈሩ።

- የቀድሞ አባቶቻችሁ በመጨረሻ አሁን ወዳላችሁበት ቦታ የመጡት እንዴት ነበር?

- ከብዙ ብዙ ዓመታት በኋላ በእግራቸውና በጀልባ ተጉዘው ነውእዚህ የመጡት።

- እንግዲህ የእናንተ ዘሮች አመጣጥ ይኸው ነበር።

- የተለያዩ የሰው ዘሮች ሁሉ አመጣጥ ይኸው ነበር።

- የቀድሞ አባቶቻችሁ በባቤል ነበሩ።

- የቀድሞ አባቶቼ በባቤል ነበሩ።

- የሰዎች ሁሉ የቀድሞ አባቶች በባቤል ነበሩ።



## ትምህርት 18

1. እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑ ሰዎችን በሙሉ ጐርፍ ልኮ እንደሚያጠፋቸው ለኖኅ ነገረው እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ነገር ይረሳል?
ለ- አይረሳም።

2. እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ሁልጊዜ ያደርጋል?
ሀ- አዎን።

3. እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን ሰዎች በእርሱ እስኪያምኑ ድረስ ለምን ያህል ጊዜ ተጠባበቀ?
ሀ- 120 ዓመታት።

4. እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ እስኪያምኑ ድረስ በሚጠባበቅበት ወቅት በእነርሱ ኃጢአት የተቆጣው ቁጣ ቀንሷል?
ሀ- አልቀነሰም።
ለ- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ፥ በኃጢአት ላይ ቁጣው እየጨመረ ነው የሚሄደው።

5. ኖኅ መርከቡን ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ እግዚአብሔር ኖኅ ምን እንዲያደርግ ነገረው?
ሀ- እግዚአብሔር ኖኅ ቤተሰቡን ይዞ ወደ መርከብ እንዲገባ ነገረው።
ለ- እግዚአብሔር ኖኅ እንስሳትንም ደግሞ ወደ መርከብ እንዲያስገባ ነገረው።

6. ኖኅና ቤተሰቡ ወደ መርከቡ የገቡት በየት ነበር?
ሀ- በአንዱ በር።

7. ሁሉም እንስሳት ወደ መርከቡ የገቡት በየት ነበር?
ሀ- በአንዱ በር።

8. ኖኅና ቤተሰቦቹ እንዲሁም እንስሳት ወደ መርከብ ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ሀ- እግዚአብሔር በሩን ዘጋው።

9. እግዚአብሔር በሩን የዘጋው ለምንድን ነው?

ሀ- በመርከቡ ውስጥ ያሉት እንዲድኑ።

ለ- ከመርከቡ ውጭ ያሉት እንዳይገቡና እንዲሞቱ።

10. ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ የሚችል አለ?

ሀ- የለም።

11. እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ ምድርን ሁሉ እንዲሸፍን ያደረገው እንዴት ነበር?

ሀ- ውኃው ምድርን በሙሉ እንዲሸፍን እግዚአብሔር ከሰማይ በላይ ያስቀመጠውን ውኃ በሙሉ አዘነበው።

12. ከዚያ በፊት ሰዎች ዝናብ አይተው ነበር?

ሀ- አላዩም።

13. ከመርከቡ ውጭ በነበሩት እንስሳት ሁሉ ላይ ምን ደረሰባቸው?

ሀ- ሁሉም ሞቱ።

14. ከመርከቡ ውጪ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ምን ደረሰባቸው?

ሀ- ሁሉም ሞቱ።

15. በመርከቡ ውስጥ ከነበሩት መካከል የሞተ አለ?

ሀ- የለም።



- የፈረንሳይኛ ቋንቋ በባቤል ተጀመረ።

- የስፓኝ ቋንቋ በባቢሎን ተጀመረ።

- ሁሉም ቋንቋዎች በባቤል ተጀመሩ።

- እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ልዩ ልዩ ቋንቋ ከሰጠ በኋላ ሌላስ ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 11፡8-9

8- ስለዚህ እግዚአብሔር፣ በምድር ሁሉ ላይ በታተናቸው፤ ከተማዋንም መሥራት አቆሙ።

9- እግዚአብሔር በዚያ የመላውን ዓለም ቋንቋ ስለ ደበላለቀ የከተማዪቱ ስም ባቤል ተባለ። ከዚያም እግዚአብሔር ሰዎቹን በምድር ሁሉ በተናቸው።

- እግዚአብሔር የተለያዩ ቋንቋዎችን ለሰዎች ከሰጠ በኋላ በምድር ወዳሉ ልዩ ልዩ ቦታዎች በተናቸው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ምድርን እንዲሞሉ ፈለገ፤ ነገር ግን ሰዎች በአንድ ስፍራ ለመኖር ፈለጉ።

- ያሸነፈው እግዚአብሔር ነው ወይስ ሰው?

- እግዚአብሔር ነው ያሸነፈው።

- ከእግዚአብሔር ጋር መታገልና ማሸነፍ የሚችል አለ?
- የለም።

- የቀድሞ አባቶቻችን ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ወሰነ።

- እግዚአብሔር ሊቀጣቸው የወሰነው በምን ነበር?

- እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ቋንቋን ሰጣቸው። ከዚህ የተነሣም አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባት አልቻለም።

- እግዚአብሔር ለሰዎች ልዩ ልዩ ቋንቋን ከሰጣቸው ሰዎች እርስ በርስ መግባባት ይችላሉ?

- አይችሉም።

- እግዚአብሔር ለሰዎች ልዩ ልዩ ቋንቋን ከሰጣቸው ረጅሙን የባቤል ግንብ መሥራትና ማጠናቀቅ ይችላሉ?

- አይችሉም።

- እግዚአብሔር ለሰዎች ልዩ ልዩ ቋንቋ ከሰጣቸው ሰዎች በአንድ ስፍራ በአንድነት መኖር ይችላሉ?

- አይችሉም።

- ከረጅም ጊዜያት በፊት አባቶቻችን አንድ ቋንቋ ብቻ ይናገሩ ነበር።

- ነገር ግን አባቶቻችን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ስላሉና ምድርን መሙላት ስላልፈለጉ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ቋንቋን ሰጣቸው።

- በባቤል እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ልዩ ልዩ ቋንቋን ሰጣቸው።

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ በባቤል ተጀመረ።



16. እግዚአብሔር ለኖኅና ለሰዎች ሁሉ የሰጣቸው ምልክት ምንድን ነው?

ሀ- ቀስተ ደመና።

17. ቀስተ ደመና የምን ምልክት ነው?

ሀ- ቀስተ ደመና እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በውኃ እንደማያጠፋ የሚያሳይ ምልክት ነው።

18. እግዚአብሔር ድፍን ምድርን በውኃ እንደማያጠፋ የገባውን ቃል ጠብቆአል?

ሀ- አዎን።

19. በምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ቅድመ አባት የሆኑት የኖኅ ልጆች እነማን ናቸው?

ሀ- ሴም ካምና ያፌት ናቸው።

- እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን ከጥፋት ውኃ ካዳነ በኋላ ብዙ ዓመታት አለፉ።

- ብዙ ዓመታት ካለፉም በኋላ ብዙ ሕዝብ በምድር ላይ ዳግመኛ መኖር እስኪጀምር ድረስ ብዙ ልጆች ተወለዱ።

- ከኖኅ በኋላ የተወለዱት ሰዎች እነማን ነበሩ?

- የእኔና የእናንተ የቀድሞ አባቶች ነበሩ።

- የቀድሞ አባቶቻች ስለ እግዚአብሔርን ያውቁ ነበር?

- አዎን።

- የቀድሞ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔርን ሊያውቁ የቻሉት እንዴት ነው?

- በመጀመሪያ ደረጃ የቀድሞ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ያወቁት፤ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ሽማግሌዎች ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጥፋት ውኃ ስለ ነገሯቸው ነበር።

- ሽማግሌዎች ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጥፋት ውኃ ለወጣቶቹ ልጆቻቸው የነገሯቸው ምን ነበር?

- ሽማግሌዎቹ ሰዎች ለልጆቻቸው እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ ከዚህ የተነሣም ኖኅና ቤተሰቡን ብቻ አስቀርቶ ሌሎችን ሰዎች ሁሉ እንዳጠፋ ነው የነገሯቸው።

- ከዚህ ሌላ፥ የቀድሞ አባቶች ስለ እግዚአብሔር ሊያውቁ የቻሉት እንዴት ነው?

- በሁለተኛ ደረጃ የቀድሞ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ያወቁት፤ ቀስተ ደመናው ስለ እግዚአብሔር ስለ ነግራቸው ነው።

- ቀስተ ደመናው ለቀድሞ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ምን ነገራቸው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን እንደሚወድድና ምድርን ዳግመኛ በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋት።

- አሁንም ከዚህ ሌላ፥ የቀድሞ አባቶቻችን ስለእግዚአብሔር ሊያውቁ የቻሉት እንዴት ነው?

- በሦስተኛ ደረጃ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ያወቁት፤ ሰማይ ተራሮች ወንዞችና ዛፎች ስለ እግዚአብሔር ስለ ነገሯቸው ነው።

- ሰማይ ተራሮች ወንዞችና ዛፎች ስለ እግዚአብሔር ምን ነገሯቸው?



- እግዚአብሔር ሰዎች የሚናገሩትን ሁሉ ያውቃል?
- አዎን።

- አንድ ሰው አንድ ነገር ከመናገሩ በፊት እግዚአብሔር ሰውየው የሚናገረውን ቃላት ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

- እግዚአብሔር የሁሉንም ሰዎች ሥራ ያውቃል?
- አዎን።

- አንድ ሰው አንድን ሥራ ከመጀመሩ በፊት እንኳ እግዚአብሔር ሰውየው ምን ሊያደርግ እንደ ሆነ ሁሉንም ነገር ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

- ሰዎች እግዚአብሔር እነርሱን እንደ ረሳ አሰቡ።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ይረሳል?

- እግዚአብሔር ሰዎች የሚያስቡትን ፈጽሞ አይረሳም።
- እግዚአብሔር ሰዎች የሚናገሩትን ፈጽሞ አይረሳም።
- እግዚአብሔር ሰዎች የሚያደርጉትን ፈጽሞ አይረሳም።

- እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ ላይ ሲያምፁ ምን አለ?

ዘፍጥረት 11፡6-7

6- እግዚአብሔር «እንዲህ እንደ አንድ ሕዝብ አንድ ቋንቋ በመናገር ይህን ማድረግ ከጀመሩ፣ ከእንግዲህ ያቀዱትን ሁሉ ማከናወን አያዳግታቸውም።
7- ኑ እንውረድ፤ እርስ በርሳቸውም እንዳይግባቡ ቋንቋቸውን እንደባልቀው።»

- ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ወደ ባቤል ሄዱ እና በዚያም ረጅም ግንብ መገንባት ጀመሩ።

- ሰዎች በባቤል ረጅም ግንብ መገንባት ለምን ፈለጉ?
- ሰዎች እጅግ ስለ ታበዩ።

- ሰዎች የራሳቸውን ስም ማስጠራት ስለ ፈለጉ።

- ሰዎች ረጅም ግንብ መሥራት መጀመራቸውን እግዚአብሔር አይቷል?
- አዎን።

ዘፍጥረት 11፡5

5- እግዚአብሔር ግን ሰዎቹ ይሠሩ የነበሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ።

- እግዚአብሔር ሰዎቹ ረጅም ግንብ እየሠሩ መሆናቸውን አየ።
- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያያል።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው በሁሉም ቦታ ያያል።
- እግዚአብሔር ሁላችሁንም ሁልጊዜ ያያል።

- እግዚአብሔር የሁሉንም ሰው አስተሳሰብ ያውቃል?
- አዎን።

- አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ከማሰቡ አስቀድሞ እግዚአብሔር የሰውየውን አሳብ ሙሉ በሙሉ ያውቃል።



- እግዚአብሔር ብቻ አምላክ መሆኑን ሰዎችም እርሱን ብቻ መከተል እንደሚገባቸው ነገሯቸው።

- ቀስተ ደመና ዛሬም ስለ እግዚአብሔር ይነግረናል?
- አዎን።

- ሰማይ ተራሮች ወንዞችና ዛፎች ዛሬም ስለ እግዚአብሔር ይግሩናል?
- አዎን።

- ስለ እግዚአብሔር ቢያውቁም ከቀድሞ አባቶቻችን ብዙዎች በእግዚአብሔር ያምኑ ነበር?

- አልነበረም።
- ከቀድሞ አባቶቻችን መካከል በእግዚአብሔር ያመኑት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ።

- ከቀድሞ አባቶቻችን ብዙዎቹ እግዚአብሔርን ከመከተል ይልቅ የተከተሉት ማንን ነበር?

- አብዛኛዎቹ የቀድሞ አባቶቻችን የተከተሉት ሰይጣንንና የእርሱን የውሸት ሃሳብ ነበር።

- አብዛኛዎቹ አባቶቻችን በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ነበሩ።

- ሰይጣን አባቶቻችን ምን እንዲያደርጉ ነበር የነገራቸው?

- ሰይጣን አባቶቻችን ለፀሐይ ለጨረቃና ለክዋክብት መስዋዕት እንዲያቀርቡ ነገራቸው።

- ሰይጣን አባቶቻችን ለዛፎች፥ ለወንዞችና ለሙታን መናፍስት እንዲሠዉ መስዋዕት እንዲያቀርቡ ነገራቸው።

- ሰይጣን አባቶቻችን እንጨትና ድንጋይ በሰውና በእንስሳት መልክ በመቅረጽ ለእነርሱ መስዋዕት እንዲያቀርቡ ነገራቸው።

- ሰይጣን አባቶቻችን በእግዚአብሔር እንዳያምኑ አሳታቸው።

- ሰይጣን አባቶቻችን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ መራቸው።

- ሰይጣን አባቶቻችን ለፀሐይ ለጨረቃና ለከዋክብት መስዋዕት እንዲያቀርቡ መራቸው።

- ሰይጣን አባቶቻችን ለዛፎች፥ ለወንዞችና ለሙታን መናፍስት እንዲሠዉ መራቸው።

- ሰይጣን ማንም እግዚአብሔርን እንዲያመልክ አይፈልግም።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔር እንዲመራቸው አልፈለጉም።

- አባቶቻችን ሰይጣንና ሌሎችን ሰዎች መከተልን ብቻ ፈለጉ።

- ከጥፋት ውኃ በኋላ አባቶቻችን የተከተሉት አንድ ሰው ናምሩድ ይባላል።

- ናምሩድ ሰዎች ብዙ ከተሞችን እንዲሠሩ አዘዛቸው።

- ሰዎች ከሠሯቸው ከተሞች አንዱ ባቤል ነበረ።

- ናምሩድ በባቤል ከተማ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ ረጅም ግንብ እንዲሠሩ አዘዛቸው።

ዘፍጥረት 11፡1-4



1- በዚያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ የሚናገሩትና የሚግባቡበት ቋንቋ አንድ ብቻ ነበር።

2- ሰዎቹም ምሥራቁን ይዘው ሲጓዙ፣ በሰናዖር አንድ ሜዳ አግኝተው በዚያ ሰፈሩ።

3- እነርሱም እርስ በርሳቸው «ኑ፣ ጡብ እንሥራ፤ እስኪበቃውም በእሳት እንተኩሰው» ተባባሉ። በድንጋይ ፈንታ ጡብ፣ ለማያያዣም ቅጥራን ተጠቀሙ።

4- ከዚያም «ለስማችን መጠሪያ እንዲሆንና በምድር ላይ እንዳንበተን፣ ኑ፤ ከተማና ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለራሳችን እንሥራ» አሉ።

- እግዚአብሔር ለአዳምና ለኖኅ ምድርን እንዲሞሏት እና በምድር ላይ በልዩ ልዩ ቦታዎች እንዲኖሩ ነገራቸው።

- እግዚአብሔር ከኖኅ በኋላ ላሉት ሰዎች እንኳ ሳይቀር ምድርን እንዲሞሏትና በምድር ላይ ባሉት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ እንዲኖሩ ነግሯቸው ነበር።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ በአንድነት በአንድ ስፍራ እንዲኖሩ ያልፈለገው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ሰዎች በአንድነት በአንድ ስፍራ እንዲኖሩ ያልፈለገው፥ እግዚአብሔርን እንዳይረሱ ስለ ፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች በአንድነት በአንድ ስፍራ እንዲኖሩ ያልፈለገው ኃጢአታቸው ብዙ እንዳይሆን ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ምድርን እንዲሞሏት ፈለገ ሰዎች ግን በአንድ ስፍራ መኖርን ፈለጉ።

- ሰዎች በዓለም ላይ በተለያዩ ቦታዎች መኖርን አልፈለጉም።

- ሰዎች በአንድ ላይ በአንድ ስፍራ መኖርን ፈለጉ።